# ሰሞነኛ ልዩ ዕትም

**«የዴሞክራሲያዊ ምርጫ**

**ግቡ ዕድገት መደላድሉም ሰላም ነው፡፡»**

## በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ

## ጄኔራል ጽ/ቤት

**የካቲት /2002**

**February/2009**




**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: 213 365 - 6651 Fax: 213 365 - 6670**

www.ethioconsulatela.org

# የዴሞክራሲያዊ ምርጫ

# ግቡ ዕድገት መደላድሉም ሰላም ነው።

የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመከተል የወሰኑ አገራትና ህዝቦች ሊያሟሉ ይገባቸዋል ተብለው የሚጠቀሱ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም፣ ዜጎች ሊመሩባቸው የሚገባውን ህገመንግስትና ከዚህ ተጨልፎ የሚዘጋጁ መመሪያዎችና ደንቦች የዜጎችን ሰብዓዊና ዴምክራሲያዊ መብቶችን የሚያረጋግጡና ዋስትና የሚሰጡ መሆናቸው የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ ብሎም መደላድል ናቸው።

የኢፌድሪ ህገመንገስት የአገራችን ዜጎች በነፃና በፈለጉት መልክ የመደራጃትና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የማድረግን ጉዳይ ከመነሻው ያረጋገጠ በመሆኑ፣ህገመንግስቱ ከፀደቀበት ማግስት ጀምሮ በርካታ ፖለቲካዊ ድርጅቶች ተቋቁመዋል። እነዚህ ድርጅቶች እንደየራሳቸው ጥንካሬና ጉድለት አዲስ የጀመርነውን የዴሞካራሲ ስርዓት ባህሪያዊ አቅጣጫ በማመልከት ረገድ በጎ አስተዋፅኦ ነበራቸው፣ አላቸውም ። ከዚህም በመነሳት አገራችን የመድበለ ፓርቲ ስርዓት የምትከተል አገር መሆኗን ይሄው የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ በይፋ አስመስክሯል።

አንዳንድ ፖለቲካዊ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ ተሳትፎን ወደ ጎን በመተው የጥላቻ ፖለቲካና ህጋዊ ያልሆነ አቋራጭ የስልጣን መንገድ በመምረጣቸው በዴሞካራሲያዊ ሂደት ጉዟችን ላይ ጠባሳ ማሳረፉ የሚዘንጋ አይደለም። ይሁን እንጅ ለረዢም ጊዜያት በፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስር ሲማቅቅ የነበረ ህዝብና አገር በመሆናችን የሚገጥሙንን ፈተናዎች በስልትና በአንስተኛ ኪሳራ በመሻገር ሰፊ ትምህርትና ተመክሮ ያገኘንባቸው ሆነው አሁን ካለንበት የተሻለ መረጋጋትና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ላይ አድርሶናል።

የኢፌድሪ ህገመንገስት በአገራችን የስልጣን ሽግግሮች በነፃና ዴሞካራሲያዊ በሆነ ህዝባዊ ምርጫን በመከተል የሚፈፀም  እንደሆነ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

ይህን መሰረት አድርጎም እ.ኢ.አ 1988 ጀመሮ በህግ በተቀመጠው መሰረት በየአምስት አመቱ የፌዴራል የህዝብ ተወካዮችና ፌደሬሽን ም/ቤት አባላትንና የክልል ም/ቤት አባላትን በመምረጥ የስልጣን ሽግግሮች ሰላማዊ በሆነ መልክ ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

እ.ኢ.አ በ1997 የአገር አቀፍና የክልል ም/ቤቶች ምርጫ በተመሳሳይ መልክ የተከናወነ ቢሆንም፣ ሰላማዊና የአመፃ መንገድን ደበላልቀው ለመጠቀም የሚፈልጉ ድርጅቶችና ግለሰቦች የለኮሱት አለመረጋጋት የዴሞክራሲአዊ ሀዲዱ ፈር እንዲለቅ የተሞከረ ቢሆንም፣ በወቅቱ ሊከተሉ የሚችሉ አስቃቂ ጥፋቶችን ለማምከን መንግስትና ህዝቡ በመረባረባቸው የዴሞካራሲ ጉዟችን ከተቃጠባት የጥፋት ደባ ሊድን ችሏል፡፡

ይህ የ1997 የጥፋት አካሄድ እንዳይደገም ፖለቲካ ደርጅቶች ሰላማዊ ፣ነፃና ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ ያላንዳች ሳንክ እንዲያከናውኑ የምርጫ ስነምግባር ማዘጋጀት አስፋለጊ ብቻ ሳይሆን የህግ የበላይነትን ማስከበሪያ መንገድም ነበር፡፡በዚህ የምርጫ ስነምግባር በማርቀቅም ሆነ  በረቀቀው ህግ በማዳኘት በኩል አሁንም ከግራ ቀኝ የሚላጉ ጥቂት ፖለቲካ ድርጅቶች ቢኖሩም ፣አብዛኞች ለደንቡ ተገዢ መሆናቸውን በፊርማቸው አረጋግጠዋል፡፡

በምርጫ ስነምግባሩ የፖለቲካ ደርጅቶች በተሰማሙበት መስርት የዚህ ዓመት ምርጫ ክርክር ተጀምሯል፡፡ ክርክሩ በየጊዜው በሚመረጡ አንኳር ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሸከረከር ሆኖ ፣ ብንመረጥ የሚከተሉትን ጉዳዮች እንፈፅማለን በማለት የድርጅቶች የፖሊሲ ጭብጦች ለኢትዮጵያ ህዝብ በሬድዮና ቴሌቬዥንን በመቅረብ ላይ ናቸው፡፡

ሁሉም ፖለቲካ ድርጅቶች ሊያሰራ የሚችልና ህዝብን የሚጠቅም የፖሊሲ ጭብጥና ሰነድ ኖራቸውም አልኖራቸው የምርጫ ክርክሩን በሚያምኑበት ሁኔታና ስነምግባር በተሞላበት መልክ ማካሄድ መቻላቸው ራሱ ለዴሞክራሲ የምናደርገው እንቅስቀሴና ትግል ማጎልበቱ አሌ አይባልም።

ከሚቀርቡት የክርክር ጭብጦች ህዝቡ የሚጠቅመውንና የሚበጀውን በማንጣለል የራሱን ድምዳሜ ይወስዳል። በዘላቂ ለአገራችን የልማት ዕድገትና ማህበራዊ ለውጥ ሊጠቅሙ የሚችሉ አካላትንና ድርጅቶች ማንነታቸውን ይበልጥ ማወቅ ይጠቀምበታል። ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ግቡ ልማትና መደላደሉም ሰላም በመሆኑ ይሄው የሁሉም ፓሪቲዎች መመዘኛ እንደሚሆን ዕምነታችን የመሆኑን ያህል ህዝባችንም ፖለቲካ ፓርቲዎችን የዓለማ ብርታት የፖለቲካ ሀሳባቸውን አዋጭነት በአጠቃላይ ብስሉን ከተቀሊሉ የሚለካበት ሚዛን ነው።

በውጭ የምንገኘው ኢትዮጵያውያን በአካል በምንኖርበት ቦታ የተነሳ በቀጥታ በምርጫው መሳተፍ ዕድላችን አናሳ ቢሆንም፣ በአገራችን የሚካሄዱትን የምርጫ ሂደቶች ዴሞክራሲያዊ ባህሪ በማላበስና የነውጠኝነትን አዝማሚያዎች በመቃወም በኩል አስተዋፅኦ ልናደርግ ይገባል ። የምርጫው ሂደትና ውጤት ሰላማዊ ፣ነፃና ታዓማኒነት ያለው ለማድረግ በሚደረጉ ተግባራት በመሳተፍ በአገራችን የዴሞክራሲያዊው ለውጥ አካል መሆን ይቻላል።